***የወንዶ ገነት ሕዝቦች ሕዝበ ውሳኔ***

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በምርጫ ህጉ አንቀጽ 27 የተለያዩ የምርጫ ዓይነቶችን እንደሚያካሂድ ይደነግጋል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ የሕዝበ ውሳኔ ነው። ይህም ሕዝቦች ፍላጐታቸውን ወይም ፍቃዳቸውን የሚገልፁበት አሠራር እና የሕዝብ ፍላጐት በመለካት አስፈላጊውን ውሳኔ ለመስጠት የሚረዳ እንደሆነ በተሻሻለው የምርጫ ህግ 532/01 አንቀጽ 32 መሠረት ተደንግጓል።

በመሆኑም ሕዝበ ውሳኔው በቅድሚያ በወንዶ ገነት ወረዳ ላይ እንዲካሄድ የፌዴሬሽን ምክር ቤት እና የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ከሁለቱም ክልሎች መስተዳድሮች ጋር ስምምነት ተደርሷል።

በዚህም መሠረት ቦርዱ ለሕዝበ ውሳኔው መልስ ለመስጠት ይረዳ ዘንድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በሕዝበ ውሳኔው አፈጻጸም ማብራሪያና የጊዜ ሰሌዳ ላይ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ግብአት ወስዷል። በመቀጠልም በጊዜ ሰሌዳ ላይ አስፈላጊውን ግብአቶች በማካተትና በማጽደቅ ወደ ትግበራ ገብቷል።

***ሕዝበ ውሳኔ ህግ ማዕቀፍ-***

**አንቀጽ 32- 532/01**

፩/ በህገ መንግሥቱ መሠረት አግባብ ባለው አካል ሲወሰን የሕዝብን ፍላጎት ለመለካት ወይም ለመወሰን ድምፅ የሚሰጥበት ሥርዓት ነው።

፪/ ሕዝበ ውሳኔው እንዲካሄድ የሚወስነው አካል በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ቦርዱ ሕዝበ ውሳኔ ያስፈለገበትን ጉዳይ ለመለየት በሚያስችለው መልኩ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን በማደራጀት ሕዝበ ውሳኔውን ያከናውናል።

፫/ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

በዚሁ አዋጅ መሠረት ለሕዝበ ውሳኔ ድምፅ ሰጪነት የሚያስፈልጉት መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው።

***በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁ መመዘኛዎች***

- ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነ/የሆነች፣
- በአማራ ዞን ሥር በሚገኙ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ውስጥ ነዋሪ የሆነ/የሆነች፣
- በምዝገባው ዕለት ዕድሜው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ/የሆነች፣
- በቀበሌው 6 ወር የኖረ/የኖረች፣
- የሕዝበ ውሳኔ ተመዝጋቢው በመደበኛነት ነዋሪ መሆኑን እና ማንነቱን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ የሚች/የምትል፣
- አስፈጻሚዎች የተመዝጋቢውን ነዋሪነት ማረጋገጥ አለባቸው።

***በድምፅ ሰጪነት ሊመዘገቡ የማይችሉ***

- ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያልሆነ/ያልሆነች፣
- በምዝገባው ዕለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ/የሆነች እና በድምፅ መስጫ ጣቢያው ከ6 ወር በታች የኖረ/የኖረች፣
- በአእምሮ ህመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌለው/የሌላት መሆኑ ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠበት/የተረጋገጠባት ሰው፣
- የመምረጥ መብቱ/መብቷ በህግ ወይም አግባብ ባለው ህግ መሠረት በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገደበበት/የተገደበባት ሰው ናቸው።

### *ሕዝበ ውሳኔ ቅድመ ዝግጅት*

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ወደ ሕዝበ ውሳኔው ከመግባቱ በፊት ለሕዝበ ውሳኔው የሚያስፈልጉ የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን አከናውኗል። በአጠቃላይ ለሕዝበ ውሳኔው አፈፃፀም የሚያስፈልገውን በጀት በዝርዝር አዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በማቅረብ እንዲፀድቅ አድርጓል። በጠቅላላው በፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕዝበ ውሳኔ እንዲካሄድ በታዘዘባቸው 3 ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች ላይ ሕዝበ ውሳኔውን ለማስፈፀም ብር 1,426,885.03 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰድስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አምስት በር ከዜሮ ሶስት ሣንቲም) ተፈቅዷል።

ሕዝበ ውሳኔውን ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን ዝርዝር ማብራሪያ አዘጋጅቶ በሚፈለገው መጠን እንዲታተም እና ከጊዜ ሰሌዳው ጋር አያይዞ ለሚመለከታቸው የሕዝበ ውሳኔ አስፈፃሚ አካላት እንዲሁም ለፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እና ለሁለቱም የክልል መስተዳድር ፕሬዚዳንቶች እንዲደርስ አድርጓል።

### *ጊዜ ሰሌዳ*

ከጥቅምት 15 እስከ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. የሕዝበ ውሳኔ ድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ በየምርጫ ጣቢያው ተካሂዷል። ጥቅምት 30 ቀን 2001 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 12፡00 ድረስ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት በየምርጫ ጣቢያው ሰላማዊ በሆነ መልኩ የሕዝብ ታዛቢዎች እና የክልል ወኪሎች በተገኙበት ተካሂዷል። በዚሁ መሠረት ከስልጠና ጀምሮ እስከ ምርጫ ውጤት ማጽደቂያ ድረስ ያለው የሕዝበ ውሳኔ አፈፃፀሙ ሂደት የሚከተለውን ይመስላል።

| ተ.ቁ | ክ ን ው ን | ቀን |
|---|---|---|
| 1 | ለሕዝበ ውሳኔ አስፈፃሚዎች ስለ አፈፃፀሙ በማዕከል ሥልጠና የሚሰጥበት | ጥቅምት 8 እና 9 ቀን 2001 ዓ.ም. |
| 2 | የድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት ስለ ድምፀ ውሳኔ አሰጣጥ ለሕዝቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ | ጥቅምት 14 ቀን 2001 ዓ.ም. |
| 3 | ለሕዝበ ውሳኔው የድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ የሚፈፀምበት | ከጥቅምት 15 - 21 ቀን 2001 ዓ.ም. |
| 4 | የመራጮች መዝገብ ለሕዝብ ክፍት ሆኖ የሚቆይበት | ከጥቅምት 22-26 ቀን 2001 ዓ.ም. |
| 5 | በድምፅ ሰጪዎች አመዘጋገብ ሂደት ቅሬታ ካለ አቤቱታ የሚቀርብበት | ከጥቅምት 22-28 ቀን 2001 ዓ.ም. |
| 6 | ስለሕዝበ ውሳኔ ድምፅ አሰጣጥ ሂደት ለየቀበሌው ሕዝብ በግንባር ገለፃ የሚሰጥበት | ከጥቅምት 23 ቀን 2001 ዓ.ም. |
| 7 | የድምፅ መስጫ ዕለት | ከጥቅምት 30 ቀን 2001 ዓ.ም. |
| 8 | የድምፅ ቆጠራ ውጤት በድምፅ መስጫ ጣቢያው በይፋ የሚገለጽበት | ሕዳር 1 ቀን 2001 ዓ.ም. |
| 9 | የድምፅ ቆጠራው ውጤት በብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የሚፀድቅበት | ሕዳር 7 ቀን 2001 ዓ.ም. |

### *ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች*

በቅድመ ሕዝበ ውሳኔ ዝግጅት በቦርዱ ባለሞያዎች የመስክ ጥናት አካሂደው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን መረጃ አደራጅተዋል። በዚህም መሠረት ለሕዝበ ውሳኔው ማስፈጸሚያ በወንዶ ገነት ወረዳ ውስጥ በሚገኙ 13 ቀበሌዎች ላይ ተካሂዷል። ቀበሌዎቹም የሚከተሉት ናቸው፦

1. ዩዋ
2. አሩማ
3. ኤዶ
4. ቡሣ
5. ባጃ ፋብሪካ
6. ጩኮ
7. ኢንታዬ
8. አባዬ
9. ኬላ 01
10. ወተራ ቀጨማ
11. ወሺና ሲየማ
12. ሻሻና ቀቀሌ
13. ጎቱና ኡትማ

### *የድምፅ መስጫ ቁሳቁሶች*

ለመራጮች ምዝገባ የሚያስፈለጉ የምዝገባ ካርዶች፣ መዝገቦች እና ሌሎች ሰነድና ቁሳቁሶች በሚያስፈልገው መጠን ተዘጋጅተው ለየምርጫ ጣቢያ በወቅቱ እንዲደርሱ ተደርጓል። ለድምፅ አሰጣጥ ሂደት የሚያስፈልጉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች፣ ፖስተሮች እና ሌሎች ሰነዶችና ቁሳቁሶች በሚያስፈልገው መጠን ተዘጋጅተው እና በየምርጫ ጣቢያው በተመዘገበው ሕዝብ ብዛት ልክ ታሽገው በወቅቱ ለየምርጫ ጣቢያው እንዲደርሱ ተደርጓል።

### *የሕዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች*

ሕዝበ ውሳኔውን ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን ዝርዝር ማብራሪያ አዘጋጅቶ በሚፈለገው መጠን እንዲታተም እና ከጊዜ ሰሌዳው ጋር አያይዞ ለሚመለከታቸው የሕዝበ ውሳኔ አስፈፃሚ አካላት እንዲሁም ለፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እና ለሁለቱም የክልል መስተዳድር ፕሬዚዳንቶች በወቅቱ እንዲደርስ አድርጓል።

የሕዝበ ውሳኔውን የሚያስፈጽሙ አስፈጻሚዎች ከወገንተኝነት ነፃ የሆኑ የሁለቱም ክልሎች ተወላጆች ያልሆኑ ብቃት ያላቸው 233 የምርጫ አስፈፃሚዎች ከአዲስ አበባ ከተማ እንዲመረጡ እና ተገቢው ሥልጠና ተሰጥቷቸው እና ቃለ መሃላ ፈጽመው በተመደቡበት ወረዳ እና የምርጫ ጣቢያ ጥቅምት 10 ቀን 2001 ዓ.ም. እንዲሰማሩ ተደርጓል።

የኦሮሚያ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች በሕዝበ ውሳኔ አፈፃፀም ማብራሪያው መሠረት በወረዳ ደረጃ አንድ አንድ ወኪል እና በ13ቱ ቀበሌዎች ውስጥ በሚገኙ 46 የምርጫ ጣቢያወች በእያንዳንዳቸው ላይ አንድ አንድ ወኪል በደብዳቤ እንዲያሳውቁ እና በተመደቡበት ቦታ ተገኝተው እንዲታዘቡ ተደርጓል።

በተጨማሪም ክልሎቹ ለሕዝበ ውሳኔው ድምፅ አሰጣጥ ሂደት የየራሳቸውን ምልክት እንዲመርጡ በደብዳቤ ተገልፆላቸው የኦሮሚያ ክልል ኦዳ ምልክቱ አድርጎ የመረጠ ሲሆን የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጎጆ ቤት ምልክቱ አድርጎ መርጧል።

### *የሕዝብ ታዛቢዎችና የክልል ወኪሎች ምርጫና ስልጠና*

የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎችም ከሁለቱ ክልሎች የተመደቡ ወኪሎች ጋር በመሆን ለየምርጫ ጣቢያው ነዋሪ ጥሪ በማድረግ በአጠቃላይ ስለሕዝበ ውሳኔው አፈፃፀም ሂደት ግንዛቤ ማስጨበጫ ገለፃ የተሰጠ ሲሆን በዕለቱ በየምርጫ ጣቢያው አምስት የሕዝብ ታዛቢዎች እና ሦስት ሥነ ሥርዓት አስከባሪዎች በምርጫ ህጉ መሠረት በነዋሪው ሕዝብ እንዲመረጡ ተደርጓል።

### *የመራጮች ምዝገባ እና የድምፅ ሰጪዎች መረጃ*

ቦርዱ በወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ከጥቅምት 15 እስከ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. የሕዝበ ውሳኔ ድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ በየምርጫ ጣቢያው ተካሂዷል። በዚህም 28,869 ወንዶች እና 25,938 ሴቶች በድምሩ 54,807 መራጭ ሕዝብ ተመዝግቧል። የድምፅ አሰጣጡን ሂደት በተመለከተ ለየምርጫ ጣቢያው ሕዝብ የአንድ ቀን ገለፃ ተሰጥቷል።

### *የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራ እና ውጤት አገላለጽ*

በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጡ ዕለት ከመድረሱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ምርጫ ጣቢያዎች ደህንነታቸውና ጥበቃቸው አስተማማኝ በሆነ መልኩ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የድምፅ መስጫ ዕለት መስከረም 7 ቀን 2010 ዓ.ም. በመሆኑ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለመጀመሩ የሕዝበ ውሳኔው አስፈጻሚዎች፣ የሕዝብ ታዛቢዎች፣ የነባር አስተዳደርና የቅማንት ራስ አስተዳደር ወኪሎች የመክፈቻ ቃለጉባኤ በመያዝ ከጥዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ድረስ የመራጭነት ካርድ የወሰደ መራጭ ዴሞክራሲያዊ መብቱን በመጠቀም ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና በተረጋጋ ሁኔታ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ተጠናቋል። በተመሳሳይ መልኩ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት እንደተጠናቀቀ ስለአጠቃላይ ውሎው በዝርዝር ሁሉም አካላት በተገኙበት የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ሰላማዊ ሆኖ መጠናቀቁን የመዝጊያ ቃለ ጉባኤ በመያዝ ተዘግቷል።

### *የቆጠራ ውጤት አገላለጽ*

በየምርጫ ጣቢያው የተካሄደው የድምፅ ቆጠራ ውጤት ለወረዳው የምርጫ ጽሕፈት ቤት ወዲያውኑ እንዲላክ ተደርጐ በየቀበሌው ተለይቶ የሕዝብ ታዛቢዎች እና የየክልሉ ወኪሎች በተገኙበት እንዲደመር ተደርጓል። የቀበሌ ድምር ውጤቱ መተማመኛ ለሁለቱም ክልሎች የወረዳ ወኪሎች ተሰጥቷል። ቦርዱ ሕዳር 5 ቀን 2001 ዓ.ም. ባካሄደው 70ኛ መደበኛ ስብሰባው በሕዝበ ውሳኔው በመራጭነት የተመዘገበው፣ ድምፅ የሰጠው እና በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ እንዲሁም በቀበሌ ደረጃ ሕዝቡ የሰጠው ድምፅ ትክክለኛ መሆኑን እና ሂደቱም ሕጋዊ እና ሰላማዊ መሆኑን አረጋግጦ አፅድቆታል። ዝርዝሩም ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርቧል። በዚህም መሠረት አጠቃላይ የሕዝበ ውሳኔው ውጤት ከዚህ በታች እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል።

*የውጤት መግለጫ ዝርዝር*

| መረጃው ዓይነት | ቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|
| የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር | 54,807 | |
| ድምፅ የሰጡ መራጮች ቁጥር | 53,155 | 96.99% |
| ከጠቅላላ መራጮች መካከል ወደ ኦሮሚያ ለመካለል የመረጡ ቁጥር | 19,029 | 35.8% |
| ከጠቅላላ መራጮች መካከል ወደ ደቡብ ለመካለል የመረጡ ቁጥር | 31,686 | 59.6% |
| የተሰረዘ ድምፅ | - | - |
| ዋጋ አልባ ድምፅ መስጫ ወረቀት | _ | - |

*የሕዝብ ውሳኔውን አስመልክቶ የቀረቡ ቅሬታዎችና የተፈቱበት አግባብ*

በመራጮች ምዝገባ ወቅት በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ የቀረቡት ቅሬታዎች፡-

1. እድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላቸው በመራጭነት ተመዝግበዋል፣
2. በምርጫ ጣቢያው 5 ዓመት ያልኖሩ ሰዎች በመራጭነት ተመዝግበዋል፣
3. የሌላ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በመራጭነት ተመዝግበዋል።

የሚሉ ናቸው።

አቤቱታዎች የቀረቡት፡-

4. በሻሻና ቀቀሌ ቀበሌ በምርጫ ጣቢያ 1ሀ እና 2ለ፣
5. በጩኮ ቀበሌ በምርጫ ጣቢያ 1ለ፣
6. በኢንታዬ ቀበሌ በምርጫ ጣቢያ 2ሀ።

ላይ ሲሆን በተራ ቁጥር 1 እና 3 የተጠቀሱት ቀበሌዎች ላይ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የምርጫ ጣቢየ ወኪሎች የቀረቡ አቤቱታዎች ሲሆኑ በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰው ቀበሌ ላይ በኦሮሚያ ክልል የምርጫ ጣቢያ ወኪሎች የቀረበ አቤቱታ ነው።

የቀረቡት አቤቱታዎች በምርጫ ሕጉ እና ቦርዱ ባወጣው የአቤቱታ አቀራረብ እና አፈታት ደንብ መሠረት በቅድሚያ በምርጫ ጣቢያ እና በይግባኝ በወረዳ የምርጫ ጽ/ቤት ደረጃ የሁለቱም ክልሎች ወኪሎች እና የሕዝብ ታዛቢዎች እንዲሁም በስፍራው የሚገኙ የጊዜያዊ አስተዳደር ተወካዮች በታዛቢነት በተገኙበት ታይቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲያገኝ ተደርጓል።

ከላይ ከተዘረዘረው አቤቱታዎች ሌላ በድምፅ አሰጣጡም ሆነ በድምፅ ቆጠራ ወቅት በምርጫ ጣቢያ ደረጃም ሆነ በወረዳ ደረጃ ከየትኛውም ወገን የቀረበ አቤቱታ የለም። በአጠቃላይ ሂደቱ በምርጫ ህጉ እና ቦርዱ ባወጣው ማብራሪያ መሠረት የተካሄደ መሆኑን ለመገምገም የቦርዱን አባላት የካተተ አንድ ቡድን ወደስፍራው ተንቀሳቅሶ ሂደቱ ሰላማዊ እና ህጋዊ በሆነ መልኩ መካሄዱን ካቀረበው ሪፖርት ለመገንዘብ ተችሏል።